# አዋጅ ቁጥር 590/2000

## የመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ሀሳብን በነፃ የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት የተረጋገጠ በመሆኑ፣

መገናኛ ብዙሃን በነፃነት ለመንቀሳቀስ ይችሉ ዘንድ የቅድሚያ ምርመራ ገደብ እንዳይሰጣቸው ሕገ-መንግስቱ ዋስትና የሰጠ መሆኑን በአጽንኦት በመገንዘብ፣

የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም፣ ብሔራዊ ደህንነትን፣ የህዝብ ሰላምና ፀጥታን እንዲሁም ሌሎች ተነጻጻሪ መብቶችና ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ሲባል በግልጽ በሚደነገጉ ሕጎች ብቻ ሃሳብን በነፃ በመግለጽና በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ገደቦች እንዲጣሉ የሚያዘውን ህገ መንግስታዊ መርህ በማረጋገጥ፣

በ□ጎች መሀከል በሚደረገው ነፃ የሀሳብና የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም በመገናኛ ብዙሃን የአሰራር ነፃነት ላይ መሰናክል የነበሩ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ ችግሮችን በማስወገድ በነፃ ሀሳብን የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን አስመልክቶ ያዳበርናቸውን አዎንታዊ እና ገንቢ ልምዶች የመጠበቅና ይበልጥ የማጠናከርን አስፈላጊነት በመረዳት፣

በሀ□ራችን □ሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ የሚሆነው መተኪያ የሌለ□ ታላቅ ሚና መጫወት የሚችል ራሱን በከፍተኛ ስነምግባር በማነፅ በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት የሚንቀሳቀስ ነፃና ፈርጀ ብዙ የመገናኛ ብዙሃን ሲሚናር ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣

መገናኛ ብ□ሃን በህገ መንግስቱ ለተረጋገጡ መሰረታዊ ነፃነቶችና መብቶች መከበር እንዲሁም ለሰላም፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ የቆሙ መሆኑን በመረዳት፣

መገናኛ ብዙሃን አጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ መረጃዎችን የመሰብሰብና የማሰራጨት መብት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ፣ በህዝቦች መካከል ነጻ የሃሳብና የመረጃ ልውውጥን □ሚ□መቻችና ዜጎች በነጻ መረጃና አስተያየትን ለመሰብሰብ፣ ለመቀበልና ለማስተላለፍ ያላቸውን መብት ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጡ የሚያስችላቸው ጤናማ የመረጃ ስርዓት □ልተ□□በ □ሞ□ራሲያዊ የህዝብ ውይይት መድረክ በመሆን ለሚያገለፅል ነጻ የመገናኛ ብ□ኃን መረጃዎችን የማቅረብ ግዴታ በህግ እንዲጣልባቸው ለማድረግ፣

በስራ ላይ ያለውን የኀሬስ አዋጅ በማሻሻል በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ከሚገኘ□ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ግንባታ ጋር በሚጣጣም አዲስ ህግ መተካቱ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፣

በኢትዮ□□ □□ራላዊ □ሞ□ራሲ□ዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 5/1/ መሰረት የሚከተለው □□ጿል::

# ክፍል አንድ

**□ቅላላ**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የመገናኛ የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም □ሚ□ሰ□□ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

1/ "የመገናኛ ብ□ሃን" ማለት በየጊዜ□ □ሚ□□ ህትመቶችንና ብሮድካስቶችን የሚያካትት የህትመት ስራ ነው::

2/ የህትመት ስራ ማለት መገናኛ ብዙሃንንና እንዲሁም ለህዝብ እንዲደርሱ ታስበው የሚሰራጩ የሙዚቃ ስራዎችን፣ የኦ□ዮ □ቪዴኽል □ጁም □ኦ□ዮቪዥዋል ስራዎችን ስክሎችን፣ ተውኔቶችን፣ ካርቱኖችን፣ መጽሀፍትን፣ በራሪ ጽሑፎችን፣ ፊልሞችን፣ ፖስትካርዶችን የንግድ ማስ□ወቂያዎችን፣ የዜና አገልግሎትንና ማንኛ□ም □ይነት ሌሎች ህትመቶችን የሚያካትት ሲሆን፣

ሀ/ በህግ አውጪ፣ በዳኝነትና በሕግ ፈፃሚ አካላት ታትመው የሚወጡ ይፋዊ መፅለጫዎችን፣ ማስ□□ቂ□ዎችን፣ ቃለ ጉባዔዎችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ውሳኔዎችን፣ □ጁም

ለ/ ለንግድና ለትራንስፖርት፣ ለቤት ውስጥ አገልግሎትና ለማህበራዊ □□ዮች □ስበ□ □ሚ□ተሙ □ርሞችን፣ የዋጋ ሰንጠረዦችን፣ የንግድና የቤተሰብ ማስታወቂያዎችን፣ ፖስትካርዶችን፣ ተባዝተው የሚሸጡ ስእሎችን፣ የንግድ አስተ□□ር □መታዊ ሪፖርቶችን ወይም የምርጫ ሰነዶችን፣ አያካትትም::

3/ በ□□□ው የሚወጣ ህትመት ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም

አጠቃላይ ስርጭት ያለውና በጠቅላላው ህብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የህዝብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጦችንና መፅሄቶችን የሚያካትት የህትመት ስራ ነው፡፡

4/ **"ብሮድካስተር"** ማለት የግል ወይም የመንግስት ድርጅትን ውስጣዊ ግንኙነቶችን የሚያካትትና ምድር ለምድር አስተላላፊ ትራንስሚተሮችን፣ ኬብሎችንና ሳተላይትን በመሰሉ ማሰራጫዎች አማካይነት በሬዲዮ ወይም በቴሌቭዥን የብሮድካስት መልእክት መቀበያዎች አማካይነት በክፍያ ወይም ያለክፍያ የብሮድካስት ኘሮግራሞችን በአንድ ጊዜ ህዝብ እንዲያዳምጣቸው እና እንዲመለከታቸው ወይም እንዲሰማቸው የሚያሰራጭ ሰው ማለት ነው፡፡

5/ "የመንግስት አካል" ማለት በፌዴራል □ጁም በ□ልል ሕ□መንግስት □ጁም በሌላ ሕፅ መሰረት የተቋቋመ ወይም በፌዴራል ወይም በክልል መንግስታት መኘቅር □ስዓ በየትኛ□ም እርከን ላይ የሚገኝ ወይም በፌዴራል ወይም በክልል መንፅስታት □ባለቤትነት ይዞታ ስር የሚገኝ ወይም ዋነኛ የፋይናንስ ምንጩን በቀጥ□ □ጁም በተዘዋዋሪ ከነዚሁ አካላት የሚያገኝ ወይም ተጠሪነቱ ለፌዴራል ወይም ለክልል መንግስት የሆነ ማንኛውም አካል ማለት ነው፡፡

6/ **"መረጃ"** ማለት በማንኛውም አይነት ቅርፅ የተቀናበረ ማንኛውም ሰነድ ማለት ነው፡፡

7/ **"ሰነድ"** ማለት በማንኛውም አካል በማንኛ□ም □□ □ተ□□ረ □ጁም □ተ□□□ ቢሆንም በመንግስት አካል ይዞታና ቁጥጥር ስር የሚገኝ፡-

ሀ/ ማንኛ□ም መ□□ብ □ጁል፣ በእጅ ወይም በማሽን የተጻፈ ረቂቅ፣

ለ/ ማንኛ□ም ማጁ□ሮ □ልም ማጁ□ሮ እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ □□□ □መ□□ብ ፅልባ□ ፣

ሐ/ የጎሉ ቢሆኑም ባይሆኑም ማንኛ□ም በእነዚህ ማይክሮ ፊልሞች ውስጥ ያሉ ምስሎች ቅ□፣

መ/ በኮምኘ□ተር □ጁም በሌላ በማንኛ□ም መሳሪ□ በመ□□□ □ሚታዩ፣ የሚነበቡ፣ □ሚ□መ□ □ጁም □ሚታወቁ መረጃዎችን ወይም

ሠ/ በማንኛውም ዓይነት ቅር□ □ጁም □ማስተላለ□□ □□ የሚገኝ፣ ማንኛ□ም መረጽ ያካት□ል፡፡

8/ □ፅለሰብ መረጽ ማለት ተለይቶ □ሚ□ወቅ ግለሰብን የሚመለከት ሆኖ፡-

ሀ/ የግለሰቡን የህክምና የትምህርት ወይም የአካዳሚክ፣ የስራ አገልግሎት፣ የሙያ፣ የወንጀል ታሪኩን የሚመለከት መረጃን ወይም ግለሰቡ ያደረጋቸውን የንግድ ግንኙነቶች የሚመለከቱ መረጃዎችን፣ ወይም

ለ/ የግለሰቡን ዘር፣ ብሔር፣ ማህበራዊ ምንጩን፣ □□ሜ፣ እርግዝና፣ የጋብቻ ሁኔ□ ፣ □ቆ□ ቀለሙን፣ የፍትወት ዝንባሌውን፣ አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነቱን፣ የጤና ብቃቱንና ጉድለቶቹን፣ ሃይማኖቱን፣ እምነቱን፣ ህሊናውን፣ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ልደቱን የሚመለከት መረጃን ወይም

ሐ/ □ፅለሰቡን የመለያ ቁጥሮች፣ ምልክቶች ወይም ሌላ መለያዎች፣ አድራሻውን፣ አሻራውን ወይም የደሙን አይነት የሚመለከት መረጃን፣ ወይም

መ/ ስለሌላ ፅለሰብ □ጁም ሌላ ፅለሰብ □ማእረግ እድገት፣ ሽልማት ወይም የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኝ በቀረበ ሀሳብ ላይ በሰጣቸው አስተያየቶች፣ አመለካከቶች ወይም አማራጭ ሀሳቦች ውስጥ የማይካተቱ የግል አስተያየቶቹን፣ ሀሳቦቹን ወይም ምርጫ- ቹን □ሚመለከቱ መረጃዎችን፣ ወይም

ሠ/ የአስተያየት ሰጭው ስም የተወገደበትና ግለሰቡን የሚመለከቱ ወይም ግለሰቡ የገንዘብ ድጋፍ፣ ሽልማት ወይም የማእረግ እድገት እንዲያገኝ በቀረበ ሀሳብ ላይ ሌላ ፅለሰብ የሰጣቸው የግል አስተያየቶች፣ አመለካከቶች ወይም አማራጭ ሀሳቦችን የያዘ መረጃን፣ □ጁም

ረ/ ሌላ ሰው ስለግለሰቡ ያለውን አመለካከት ወይም የሰጠውን አስተያየት የያዘ መረጃን፣ □ጁም

ሰ/ ፅለሰቡን በሚመለከቱ ግላዊ መረጃዎች ጋር የተያዘውን ወይም መግለፁ በራሱ ግለሰባዊ መረጃን የመግለጽ ውጤትን ሊያስከትል የሚችል የግለሰብ ስም የያዘ መረጃን፣ የሚያካትት ሲሆን በምንም ሁኔ□ ከሞተ ዓመት የሞላው ግለሰብን የሚመለከት መረጃን ግን አያካትትም::

9/ **"ሶስተኛ ወገን"** ማለት ከመረጃ ጠያቂው ውጪ ወይም መረጃውን ከተጠየቀው

የመንግስት አካል □ሁ□ □ሆነ ማንኛ□ም ሰ□ ወይም ማንኛውም የመንግስት አካል ማለት ሲሆን የውጪ ሀገር መንግስትን፣ መንግስታዊ አካልን፣ ድርጅትን ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም አካልን ያካት□ል::

## 10/ የጠላትና የአማጺያን እንቅስቃሴዎች ማለት፡-

ሀ/ በሀገሪቱ ላይ የተቃጣ የወረራ ድርጊት፣

ለ/ በሀገሪቱ ወይም በህዝቡ ወይም በሀገሪቱ ስትራቴጂያዊ ጥቅሞች ላይ ያነጣጠሩ የውስጥ ወይም የውጪ የአሻጥር ወይም የሽብር ተግባራት፣

ሐ/ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ወይም በአመጽ መለወጥን ዓላማው ያደረገ እንቅስቃሴ ወይም

መ/ ማንኛውም የውጭ ሀገር የስለላ ተግባራት ወይም የጠላት እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡

11/ ዋና አዘጋጅ ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 6 በተደነገገው መሰረት ሙሉ የኢዲቶሪያል ስልጣን ያለው ሰው ነው::

12/ **"አሳ□ሚ"** ማለት መገናኛ ብዙኋን የሚወክል ወይም መገናኛ ብ□ኃን ባለበት የሆነ፣ በ□ር□ቱ ውስጥ የጎላ የባለንብረትነት ጥቅም ያለው ወይም የድርጅቱን የስራ አስተዳደር የሚመራ ማንኛውም ሰው ነው::

13/ **"አ□ሚ"** ማለት የህትመት ስራዎችን ለማተም በአሳ□ሚ□ □ተሾመ □ጁም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ማንኛውም ሰው ነው::

14/ **"አከፋፋይ"** ማለት የህትመት ስራዎችን በጅምላ ለማከፋፈል በአሳ□ሚ□ □ተሾመ ወይም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ሰው ነው::

15/ **"አስመጪው"** ማለት የመገናኛ ብዙሃን ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት በማሰብ ወደ ሀገር □ሚ□ስ□ባ ወይም በሀገር ውስጥ የሚሰራጩ የውጭ ህትመቶች ወኪል የሆነ ማንኛ□ም ሰው ነው::

16/ ***"□ህ□ብ እንባ ጠባቂ"*** ማለት በአዋጅ ቁጥር 211/1992 መሰረት የተቋቋመ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ነው

17/ **"□ልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ ________መሰረት □ተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል አዲስ አበባንና □ሬዳዋን ይጨምራል፡፡

18/ **"የህዝብ ግንኙነት □ላ□"** ማለት የህዝብ ግንኙነት ስራን ለማከናወን በመንግስት አካል □ተመ□በ ወይም የተሾመ የህዝብ ግንኙነት □ላ□ □ጁም ሌላ ኃላፊ ማለት ነው፡፡

19/ "ሰ□" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

**3. ስለ□ታ አገላለጽ**

በግልጽ የተደነገገው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል::

**4. መገናኛ ብዙሃን ነፃ ስለመሆናቸው**

1/ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት በሕገ መንግስቱ ዕውቅና አግኝቷል:: ቅድመ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው::

2/ በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ገደቦች የሚጣሉት ሕገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል::

3/ ማንኛውም የመንግስት አካላት የመገናኛ ብዙሃን ማህበራዊ ተግባራቸውን ለመወጣት:-

ሀ/ ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፣

ለ/ በል□ ል□ □□ዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብ፣ ወይም

ሐ/ የተለያዩ ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የህዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሂደት የመሳተፍ፣

መብታቸውን ማክበር ይኖርባቸዋል::

4/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ/2/ መሰረት በግልፅ የተደነገጉ ህጎች ከሌሉ በስተቀር የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የሚያስተጓጉሉ ማናቸውም አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተከልክለዋል::

**5/ <u>የማሳተምና የመደራጀት ነፃነት</u>**

1/ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዜግነቱ ኢትዮ□□ዊ የሆነ ሰው የመገናኛ ብዙሃን ስራ የመስራት መብት አለው::

2/ ጋዜጠኞች በመረጡት የሙያ ማህበር ራሳቸውን የማደራጀት መብት አላቸው::

# ክፍል ሁለት

## በመገናኛ ብዙሃን ስራ የመስራት መብት

### 6. ዋና አዘጋጅ

1/ በመገናኛ ብ□ኃን ዋና አዘጋጅነት የሚሾም ሰው ስልጣን የሚታተሙትን ህትመቶች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ እንዳይታተም ማድረግን ያካትታል:: ይህን ስልጣን የሚገድቡ ማናቸውም አሰራሮች ወይም ስምምነቶች በህግ ፊት ውድቅና ፈራሽ ናቸው::

2/ የመገናኛ ብዙሃን ዋና አዘጋጅ በማንኛውም ምክንያት የተሟላ የህግ ችሎ□ የሌለው ከሆነ የተሟላ የህግ ችሎ□ □ሌለው ከሆነ የተሟላ የህግ ችሎታ ያለው ኃላፊ አዘጋጅ መሾም ይኖርበ□ል::

3/ በ□ህ አንቀጽ በንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት ለኃላፊነት የተሾመው ዋና አዘጋጅ ለመገናኛ ብዙሃን ውጤት ይዘቶች ሙሉ የህግ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ነገር ያለፍቃዱ ታትሞ እንዲ□□ □ማ□ረፅ ስልጣን አለው::

### 7. የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት

1/ ለአገር አቀፍ ወይም ቁጥሩ 100,000 በላጁ □ሆነ የተመዘገበ ነዋሪ ለሚገኝ ቤት አካባቢ □ጁም □ልል □ብሮድካስት ፈቃድ ከያዘ ኩባንያ ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ውስጥ በቀዓ□ም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤ□ማ ቁጥጥር ያለው ማንኛ□ም ሰ□ ተመሳሳጁ □ቃ□ በ□□ እና በተመሳሳይ ወይም በተደራራቢ የገበያ አካባቢ □ብሮድካስት አገልግሎት ከሚሰጥ ሌላ ኩባንያ ጠቅላላ ካፒ□ል ወይም አክስዮን ላይ በቀዓታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤ□ማ ቁዓዓር ሊኖረው አይችልም::

2/ ለአገር አቀፍ ወይም ቁጥሩ ከ100,000 በላጁ □ሆነ የተመዘገበ ነዋሪ ካለበት አካባቢ ወይም ስ□ራ □ብሮድካስት አገልግሎት ፍቃድ በያዘ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀዓ□ □ጁም በተ□ሻሻሪ □□□ማ ቁጥጥር ያለው ማንኛ□ም ሰ□ በዚሁ አካባቢ ወይም በተደራራቢ የገበያ አካባቢ □ሚሰራ□ በ□□□□ የሚወጣ ህትመት ስራን ከሚሰራ ሌላ ማንኛውም ኩባንያ ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥ□ □ጁም በተ□ሻሻሪ □□ታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም::

3/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየጊዜ□ □ሚ□□ ህትመት ስራን የሚሰራ ኩባንያ ካፒ□ል □ጁም አክስዮን ላይ በቀዓታም ሆነ

በተ□ሾሾሪ □□□ማ ቁዓዓር □ለ□ ማንኛ□ም ሰ□ በተመሳሳዱ □ጁም በተ□ራራቢ ገበያ የሚሰራጭ የህትመት ስራን ከሚሰራ ሌላ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ □□ታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም::

4/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከተው የአክስዮን □□□ማ ቁጥጥር የሚወሰንበትና □መለኪያ ቅኙቱ የሚከናወንበት ስነ ስርዓት በሕግ ተደንግጐ እስኪወ□ □ረስ ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውም ኩባንያ ወይም ድርጅት አክሲዮኖች ወይም ካፒታል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከ15 በመቶ በላጁ የያዘ ማንኛ□ም ሰ□ □□ታማ ቁጥጥር እንዳለው ይገመታል::

5/ ለዚህ አዋጅ አንቀጽ 5/1/ አፈፃፀም ሲባል አንድ ኩባንያ ኢትዮጵያዊ ኩባንያ ነው የሚባው የኩባንያው የካፒታል ምንጭ ሙሉ በሙሉ ከሀገር ውስጥ የሆነ እና የአክስዮኑ ባለድርሻዎች በሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው እንደሆነ ሲሆን የውጭ አገር ሰዎች የአክስዮኑ ባለድርሻዎች የሆኑበት ድርጅት ማህበርተኛ የሆኑበትን ኩባንያ አያካትትም:: በተመሳሳይ አንድ ማህበር የሀገር ውስጥ ማህበር ነው የሚባለው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕግ መሰረት እንደ አገር በቀል ማህበር ሲመዘገብ ነው::

6/ በህግ የሰውነት መብት ከተሰጠው አካል ወይም ድርጅት በስተቀር ማንኛውም ሰው የብሮድካስት አገልግሎት ስራን፣ በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችን ወይም የዜና አገልግሎት ስራን ለመስራት አይችልም::

7/ ሀ□ር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና ዋነኛ አትኩሮቱ በሀገር ውስጥ ጉዳዮች ላይ የሆነ ማንኛውም የውጭ ሀገር የመገናኛ ብዙሃን ላይ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ::

## 8. አከፋፋዮች

በ□□□□ የሚወጡ ህትመቶችን የማከፋፈል ስራ የሚሰሩ ድርጅቶች የህትመቶቹን ይዘት መሰረት በማድረግ የአገልግሎትም ሆነ የክፍያ ልዩነት ማድረግ የለባቸውም::

## 9. የምዝገባ የምስክር ወረቀት

1. ማንኛውም በየጊዘው የሚወጣ የህትመት ስራ □ጁም □□ና አገልግሎት ስራ ለመስራት □ሚ□ልፅ ሰ□ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 3 የተመለከቱትን መረጃዎች በማቅረብ □ም□□ባ ምስክር ወረቀት የሚያገኘ□ ስር□ ቱ ከአንድ ክልል በላይ ከሆነ ከማስ□ □ቂ□ ሚኒስቴር ሲሆን ስርጭቱ በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የተወሰነ ከሆነ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚያገኘው ከክልሉ ማስታወቂያ ቢሮ ይሆናል::

2. ማንኛ□ም አካል ወይም ድርጅት ወይም መንግስ□ዊ አካል ዓላማውን ለማራመ□ □ጁም በህግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ማሳተም ካስ□ለ□□ በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት እንደተመዘገበ ይቆጠራል።

**3. □ም□□ባ ማመልከቻው የሚከተለውን ዝርዝር መያዝ አለበት፡-**

ሀ/ □አሳታሚውን ወይም □ዜና አገልግሎት ድርጅቱን ስምና አድራሻ እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ካሉ አድራሻቸውን

ለ/ በ□□□ው የሚወጣው ህትመት ወይም የዜና አገልግሎት ድርጅቱ ስም፣ እና

ሐ/ በአሳታሚው ወይም በዜና አገልግሎት ድርጅቱ ከ2 በመቶ የበለጠ የአክስዮን ድርሻ ያላቸውን ሰዎች ስም አድራሻና የአክስዮን ድርሻቸውን መጠን።

4/ አስቀድሞ ከተመዘገበ በየጊዜው ከሚወጣ ህትመት ጋር አንድ ዓይነት □ጁም ተመሳሳጁ በሆነ ስም ወይም አርማ ሌላ በ□□□ው የሚወጣ ህትመት አሳትሞ ለማውጣት የምዝገባ ሰርተፊኬት ጥያቄ የቀረበ ከሆነና የሁለቱ ህትመቶች መመሳሰል የሚያሳስት ከሆነ በ□□□ው የሚወጣ ህትመት በሌላ ስያሜ ወይም አርማ እንዲመዘገብ ይደረጋል።

5/ □ማስ□ወቂያ ሚኒስቴር □ጁም □□ልሉ ማስ□□ቂ□ ቢሮ ማመልከቻ በቀረበለት በቀናት ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ካልተሰጠ ወይም ያልተሰጠበትን ምክንያት በጽሑፍ ለአመልካቹ ካላሳወቀ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም □□ና አገልግሎት □ንደተመ□□በ ጁቆ□ራል።

6/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ 3 በተ□ፈ□ሩት ሁኔ□ዎች ላይ ለ□ዓ ሲ□ረፅ በ□□□□ የሚወጣ ሕትመት አሳ□ሚ □ጁም □□ና አገልግሎቱ ድርጅት ለወጡ በተከሰተ በ15 ቀናት ውስጥ ለመዝጋቢው አካል የተደረገውን ለውጥ ማሳወቅ አለበት

**7/ የምዝገባ ሰርተፊኬት ሊሰረዝ የሚችለው**

ሀ/ በ□□□ው የሚወጣ ህትመት ወይም የዜና አገልግሎት ስራ ሲሆን አሳ□ሚ□ □ጁም □ርጅቱ ስራውን ማቆሙን በጽሑፍ ሲያሳውቅ □ጁም

ለ/ በ□□□□ ለሚወጣ ሕትመት ወይም የዜና አገልግሎት ስራ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ህትመቱን ማውጣት ያልጀመረ ወይም የዜና አገልግሎት ስራውን ያልጀመረ እንደሆነ ነው።

8/ የዚህ አንቀፅ የንዑስ አንቀፅ /7/ ድንጋ□ እንደአግባቡ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ ወይም ተፈጻሚ ይሆናል።

10. **በህትመት ላይ የሚገለፁ ነገሮች እና ያለ ክፍያ የሚሰጡ ቅጅዎች**

1/ ማንኛውም አይነት በየጊ□ው የሚወጣ ህትመት በእያንዳንዱ አቅም ላይ የአሳታሚውን፣ የአታሚውን፣ የዋና አዘጋጁን ስምና አድራሻ፣ የህትመቱን ቅፅ፣ ቁጥር፣ ህትመቱ የሚወጣበትን ጊ□ እና ታትሞ የወጣበትን ጊ□ እና ታትሞ የወጣበትን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ማስፈር አለበት።

2/ ማንኛውም ብሮድካስተር በእያንዳንዱ ኘሮግራም መጀመሪያና ማብቂያ ላይ የጣቢያውን ስምና ኘሮግራም፣ የኘሮግራሙን መሪ መግለፅ ይኖርበታል።

3/ ማንኛውም በአዲስ አበባ የሚሰራጭ ወይም አገር አቀፍ ስርጭት ያለው በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ታትም በወጣ ከሀያ አራት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም ሁለት ቅጂዎች ያለክፍያ ለብሄራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መፃህፍት ኤጀንሲ መስጠት አለበት።

4/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ስርጭት በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ ከሆነ ታትሞ በወጣ ከሀያ አራት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም ሁለት ቅጂዎች ያለክፍያ ለክልሉ ቤተመዛግብት ወይም ማስታወቂያ ቢሮ መስጠት አለበት።

# ክፍል ሶስት

## መረጃ የማግኘት መብት

**11. □ላማ**

በ□ህ □□ል የተደነገጉ ድንጋጌ- ች:-

1/ ተነፃፃሪ የህዝብና የግለሰብ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የወጡ ተገቢ ገደቦች □ንደተጠበቁ ሆኖ ከማንኛ□ም መንግስታዊ አካል ዜጎች መረጃን ለመጠየቅ ለማግኘት እና ለማስተላለፍ ያላቸውን መብት ተፈፃሚ የማድረግ፣

2/ መረጃ ፈላጊዎች መረጃዎችን በተቻለ መጠን በፍጥነትና በዝቅተኛ □□ ሳጁ□□ሙ □ሚ□□ኑበትን አሰራርና ስነ ስርዓት በመመስረት መብቱን ተፈጻሚ የማድረግ፣ እና

3/ የህዝብ ተሳትፎን የስልጣን ባለቤትነትን የማረጋገጥ እና እንዲሁም የአሰራር ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሰፈነበት የመንግስት አሰራርንና መልካም አስተዳደርን የማጠናከር ዓላማ አላቸው::

**12. መረጽ □ጁቆ □ማፅኘት መብት**

1/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው ከማንኛ□ም መንግስታዊ አካል መረጃን የመጠየቅ፣ የማግኘትና የማስተላለፍ መብት አለው::

2/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተመለከተው መብት መረጃውን ወይም የመረጃውን ምንጭ የያዘ ሰነድ በማንኛውም መንግስታዊ አካል እጅ የሚገኝ መሆን አለመሆኑን በመጠየቅ የማወቅ መብትንና በመንግስታዊ አካል እጅ □ሚ□ነውን ሰነድ:-

ሀ/ የመመልከት ወይም ማስታወሻዎችን የመውሰድ ወይም ጥቅሶችን የመገልበጥ፣

ለ/ ጉዳዩ በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተረጋገጠ ትክክለኛ ፅልባ□ □መ□ሰ□፣ □ጁም

ሐ/ በዲስኬቶች፣ በፍሎፒዎች፣ በሌላ በማንኛ□ም ዓይነት የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካይነት የመውሰድ ወይም ሰነዱ በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሳሪያ የሚገኝ ከሆነ ከዚሁ መሳሪ□ ታትመው የወጡ ቅጂዎችን የመውሰድ፣

3/ ይህ አዋጅ የመንግስት አካላት በአዋጁ ከተደነገጉት ስርአቶች ውጭ መረጃን የመስጠት ስልጣናቸውን እንደሚገድብ ተደርጎ መተርጎም አይኖርበትም::

03.አትሞ የማውጣት ግዴ□

1/ ማንኛውም መንግስታዊ አካል፡-

ሀ/ ስለመስሪ□ ቤቱ መዋቅር፣ አደረጃጀት፣ ስለ ዋና ተግባራቱና ኃላፊነቱ፣

ለ/ □□ላፊዎቹን ስልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆነው ስነ ስርአት፣

ሐ/ ለሕዝብ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዝርዝር

መ/ ለተ□ል□□ ህ□ብ ስለተበ□□ □ቅሬ□ አሰማም ስርአትና ከህዝብ ዘወትር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬ□ዎች የመስሪያ ቤቱን ምላሽ የሚያሳዩ አጭር ዘገባዎችን፣

ሠ/ በ□ፃ ስለሚ□ኙ መዝገቦች አይነትና በመዝገቦቹ ውስጥ ስለሚገኙ መረጃዎች ይዘት አጭር ማብራሪያ እንዲሁም መረጃ ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች የመረጃ ዓ□ቄዎች አቀራረብ ስነ ስርአት ዝርዝር ማብራሪያዎችን፣

ረ/ □መስሪ□ ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ የመስሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ አካላት ስራዎች □ሚመሩባቸውን ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች እንዲሁም የተሻሻሉ □ጁም □ተሻሩ መመሪያዎች የሚገኙባቸውን መዝገቦች ዝርዝር፣

ሰ/ □□ር□ቱ ሰራተኞች የሚሰሩባቸውን መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ማብራሪያዎችና ሌሎች ሰነዶች፣

ሸ/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው ስም እና አድራሻ፣ እና

ቀ/ ሌሎች ዝርዝሮችን አትሞ ያወጣል፡፡

2/ ማንኛ□ም የመንግስት አካል አስፈላጊ የሆነ ለውጥ ሲኖር □ተለ□ጡ ነገሮች የታከሉበትን እና በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ህትመት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በማ□ጣት ለማንኛውም ጠያቂ ወዲያውኑ የህትመቱን ቅጂ መስጠት □ጁም እንዲመለከት ማድረግ አለበት፡፡ ሆኖም እያንዳንዱ የመንግስት አካል በእነዚህ ህትመቶች ውስጥ በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት የማይገለፁ መረጃዎችን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች መሰረት መገለፅ የሌለባቸውን ነገሮች ማካተት የለበትም፡፡

**3/ ማንኛውም የመንግስት አካል፡-**

ሀ/ የህዝብን ጥቅም የሚመለከቱ ጠቃሚ ፖሊሲዎችን ውሳኔዎችን ይፋ በሚያደርግበት □□ ከውሳኔዎቹ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በሙሉ አትሞ ማውጣት አለበት፡፡

ለ/ የአስተዳደራዊ፣ የዳኝነትም ሆነ የዳኝነት ነክ ውሳኔዎችን ሲሰጥ የሂሳብ ልዩነት ካለም ከነልዩነቱ ለማንኛውም መረጃ ጠያቂ የህትመቱን ቅጂ መስጠት ወይም እንዲመለከተው ማድረግ አለበት፡፡

ሐ/ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆዎች መሰረት ማንኛውም አይነት ኘሮጀክት ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ለጠቅላላው ህዝብ ወይም ጥቅማቸው ለተነካባቸው ወይም ሊነካባቸው ለሚችሉ ወገኖች ከፐሮጀክቱ ጋር የተያያዙ ፍሬ ነገሮችን አትሞ ማውጣት ወይም ማሳወቅ ይኖርበ□ል፡፡

**14/ *መረጃ ለማፅኘት ስለሚቀርቡ ጥያቄዎች***

1/ መረጃ ለማፅኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፣ የሚፈልገውን መረጃ ለይቶ በመግለጽ ጥያቄውን በጽሑፍ ወይም ሊነበብ በሚችል የኤሌክትሮኒክስ ዘ□ አማካይነት ለዚህ ዓላማ በ□መስሪ□ ቤቱ □ተ□□□ን የመጠየቂያ □ርም በመሙላት ለሚመለከተው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡ መረጃ ጠያቂው ማንበብና መጻፍ የማይቻል ከሆነ □ይም በአካል ጉዳት ምክንያት ጥያቄውን በጽሑፍ ማቅረብ ካልቻለ የህዝብ ግንኙነት □ላ□□ በተ□□□□ □ርም ላይ በመሙላት መተባበር አለበት፡፡

2/ □መረጃ ዓ□ቄ ያቀረበ ማንኛውም መረጃ ፈላጊ መረጃውን የፈለገበትን ምክንያት መጠየቅ የለበትም፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ/1/ መሰረት □መረጃ ዓ□ቄ □□ረሰው የህዝብ ግንኙነት □ላ□ በተቻለ ፍጥነት ሆኖም በማንኛውም ሁኔ□ ከ30 የስራ ቀናት ባልበለ□ □□ □ስዓ የተጠየቀውን መረጃ በክፍያ ለአመልካቹ መስጠት ወይም በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ሶስት ክልከላን በተመለከተ የተደነገጉትን ምክንያቶች በመጥቀስ የመረጃ ጥያቄውን ያልተቀበለው መሆኑንና ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን በመግለፅ ምላሹን በፅሑፍ መስጠት አለበት፡፡

4/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው አመልካቹ የተተመነውን ክፍያ በመክፈል መረጃውን እንዲወስድ ከተወሰነ ለመረጃ ጠያቂው የክፍያውን መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔ□ □ር□ሮ ክፍያውን እንዲፈጽም በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማስታወቂያው በተላከበትና ክፍያው በተፈጸመበት ቀን መካከል ያለው ጊ□ በላጁኛ□ ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው የ30 □ስራ ቀን ጊዜ ውስጥ አይካተትም፡፡

5/ በንዑስ አንቀጽ /3/ በተመለከተ□ □□ □ስዓ ለመረጃ ዓ□ቄ□ ምላሽ አለመስጠት ዓ□ቄውን እንዳለመቀበል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

6/ የመንግስት አካልን የሰውንና የቁሳቁስ ኃይል ያለአግባብ እንዲባክን ወይም መደበኛ ተፅባሩን የሚያስት ወይም ለመዝገቡ የጥበቃ ደህንነት አስ□□ ካልሆነ በስተቀር መረጃው መስጠት ያለበት ጠያቂው ይሰጠኝ ባለበት □ይነት □ርም ነው፡፡

7/ ማንኛ□ም □መስሪ□ ቤቱ □ላ□ □ጁም ሰራተኛ በህዝብ ግንኙነት □ላ□□ □መረጃ ዓ□ቄ ሲቀርብለት የመተባበር ፅ□□ አለበት፡፡

8/ በመስሪ□ ቤቱ ሰነድ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ለማፅኘት ጥያቄ የቀረበለት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /3/ የተመለከተውን የሰላሳ ቀን □□ ለተፊ ማሪ □ስራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም የሚችለው፡-

ሀ/ መስሪ□ ቤቱ በበርካ□ ተመሳሳይ የመረጃ ጥያቄዎች የተጥለቀለቀ ከሆነ እና የተጠየቀውን መረጃ የስራ ቀናት ውስጥ ለመስጠት የማይቻል አጠቃቀም የሚያዛባ ከሆነ፣

ለ/ መረጃውን በተወሰነ□ □□ ለመስጠት በርካታ ሰነዶችን ማገላበጥ የሚያስፈልፅ በመሆኑ □ስ□ ኃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀም የሚያዛባ ከሆነ፣

ሐ/ የተጠየቀውን መረጃ የመፈለጉ ወይም የማሰባሰቡ ወይም የማጠናቀሩ ስራ በተለ□□ ከተሞች ውስጥ ከሚገኙ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች የሚገኙ በርካታ መዛግብትን መመልከትን የሚጠይቅ ከሆነና ወይም በ30 ቀናት የስራ ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ የማይችል ከሆነ

መ/ የተፈለገውን መረጃ ለመስጠት ከመንግስት አካል ልዩ ልዩ አካሎች ወይም ክፍሎች □ጁም □ልሎች መንግስታዊ አካላት ጋር መመካከሩ ተገቢ ወይም አስፈላጊ ከሆነ እና በዚህ የተነሳ መረጃውን በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ፣ ወይም

ሠ/ ተ□□ቂ□ ራሱ □□□ ቢራ□ም □ቃ□ኛ መሆኑን በጽሑፍ የገለጸ ከሆነ፣

9/ በ□ህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ /3/ የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም የመንግስት አካል አጣዳፊ ለሆነ ጉዳይ የመረጃ ጥያቄ ሲቀርብለት እጅግ ቢዘገይ ከአስር የስራ ቀናት ባልበለ□ □□ ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

10/ በመንግስታዊ አካላት አጣዳፊ ወይም አስቸኳይ ተብለው በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አጣዳፊ ወይም አስቸኳይ ጉዳይ እንዳለ የሚቆ□ረ□፡-

ሀ/ የተጠየቀው መረጃ በአስቸኳይ ካልተሰጠ በሰው ሕይወት ወይም አካላዊ ደህንነት ላይ □ቅርብ □□ አደጋን ሊያስከትል ይችላል የሚያሰኝ ተጨባጭ ምክንያት መኖሩን የሚያሳይ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ፣ወይም

ለ/ መረጃን ለህዝብ ማሰራጨት ዋነኛ ተፅባሩ በሆነ አመልካች በመንግስት አካል ተከናውኗል ወይም ሊከናወን ነው የሚባልና ህዝብ በአስቸኳይ ሊያውቀው ይገባል የሚያሰኝ ተጨባጭ ምክንያታዊ መነሻ ያለው ጥያቄ □ቀረበ እንደሆነ፣ ነው፡፡

11/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ /10/ /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት □ቀረበ□ □መረጃ ዓ□ቂ አጣዳፊ አይደለም ብሎ ካመነ አመልካቹ አስተዳደራዊ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑን በመግለፅ ምላሹን በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀፅ /9/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ □ር□ ቤት በዚህ መሰረት ምላሽ የተሰጠበትን ጉዳይ በይግባኝ ሊመረምር አይችልም፡፡

02/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት መረጃ ለማግኘት የሚከፈለው ክፍያ መረጃውን የያዘውን ሰነድ ለመፈለግ፣ ለማሰባሰብና ለማባዛት ከሚያስፈልገው ወጪ መብለጥ የለበትም:: ሆኖም የግል መረጃን ለማግኘት ጥያቄ የሚያቀርቡ አመልካቾች ወይም □መ□□ል አቅም የሌላቸው ጠያቂዎች እንዲከፍሉ መደረግ የለባቸውም::

## 16/ የማይገለጹ መረጃዎች

1/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 02 የተመለከተው መረጃ የማግኘት መብት በዚህ ክፍል ስር በተደነገጉ ገደቦች ካልሆነ በስተቀር መረጃ እንዳይገለፅ በሚከለክሉ ማንኛ□ም □ህፅ ክልከላዎች ሊገደብ አይችልም::

2/ በ□ህ □□ል ስር በተደነገጉ የማይገለፁ መረጃዎች ውስጥ የማይሸፈን ማንኛ□ም መረጽ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ምስ□ር ነው ተብሎ በመፈረጁ ብቻ በዚህ አዋጅ የተረጋገጠውን መረጽ □ግፅኘት መብት አፈፃፀም ሊያስቀር አይችልም::

## 16. ሶስተኛው ወገንን የሚመለከቱ የግል መረጃዎች

1/ ማኛውም ህዝብ ግንኙነት □ላ□ ከሞተ 1 ዓመት ያልሞላውን ሰው ጨምሮ □ሶስተኛ ወገንን የግል ሕይወት የሚመለከቱ መረጃዎች ያለበቂ ምክንያት እንዲገለፁ የሚያደርፅ ከሆነ የቀረበውን የመረጃ ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ይችላል::

2/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሰረት ሶስተኛ ወገንን የሚመለከተውን መረጃ ለመከልከል የማይቻለው:-

ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀ□ 19 መሰረት ሶስተኛው ወገን የመረጃውን መግለፅ ያልተቃወሙ ከሆነ ወይም መረጃውን ለጠየቀው ሰው እንዲገለፅ ፈቃደኝነቱን በጽሑፍ የገለጸ ከሆነ፣

ለ/ መረጃውን የሰጠው ሶስተኛ ወገን መረጃውን በተቀበለው የመንግስት አካል ወይም በርሱ ስም መረጃውን በተቀበለው ሌላ ወገን አማካይነት የሚሰጠው መረጃ ለህዝብ ግልጽ የሚደረግ መሆኑን ወይም ግልፅ ሊደረግ የሚችል መሆኑን አስቀድሞ እንዲያውቀው ተደርጎ ከሆነ፣

ሐ/ መረጃው አስቀድሞ ለሕዝብ ግልጽ ተደርጎ ከሆነ

መ/ መረጃው የግለሰብን የአ□ምሮና የአካል ምንነት ወይም ደህንነት የሚመለከት ከሆነና መረጃው የሚመለከተው ሰው በመረጃ ጠያቂው ሞግዚትነት ስር የሚተዳደር ከሆነ፣ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ከሆነ ወይም የጥያቄውን ፀባይ ለመረዳት የማይችል ከሆነና መረጃውን መስጠቱ ለሶስተኛው ወገን ጥቅም አስፈላጊ ከሆነ፣

ሠ/ መረጽ□ በህይወት የሌለ □ሶስተኛ ወገንን የሚመለከት ከሆነና የሚቹ የቅርብ የስጋ ዘመድ በሆነ ሰው መረጃው እንዲገለጽ ከጠየቀ ወይም የሚቹን □ስ□ □መ□ □□ሑ□ □ቃ□ በያዘ ሰው አማካይነት መረጃው እንዲገለጽ ጥያቄ የቀረበ ከሆነ ወይም

ረ/ □ተ□□ቀ□· መረጃ በመንግስት መስሪያ ቤት የሚሰራን ወይም ይሰራ የነበረን ሰው የስራ ኃላፊነትና ደረጃን ጨምሮ ማዕረጉን፣ የስራ አድራሻውን፣ የመስሪያ ቤት ስልክና ተመሳሳዷ □ር□ር አድራሻውን፣ የስራ መደቡን፣ ደመወዙንና ሌሎች ክፍያዎቹን፣ ወይም የግለሰቡን የስራ □ላፊነቶችና፣ በስራው ላይ ያከናወናቸውን ተግባሮች ወይም ፅለሰቡ ራሱ በሞላ□· መዝገብ ላይ ያሰፈረውን ስሙን የሚመለከት ከሆነ፣ ነው፡፡

17. □ኦስተኛ ወገንን የንግድ መረጃዎች ስለመጠየቅ

1/ የሕዝብ ግንኙነት □ላ□□· □ተ□□ቀ□· መረጃ:-

ሀ/ □ኦስተኛ ወገን የንግድ ምስጢር የያዘ ከሆነ፣

ለ/ የንግድ ምስጢር ባጁሆንም የሶስተኛ ወገንን የፋይናንስ፣ የንግድ፣ የሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ መረጃዎችን የሚመለከት ከሆነና የመረጃዎች መ□ለ□ በሶስተኛው ወገን የፋይናንስ □ጁም የንግድ ጥቅሞች ላይ ጉዳትን የማስከተል ውጤት የሚኖረው ከሆነ፣ □ጁም

ሐ/ ለሌላ □ንደማይገለጽበት በማመን በሶስተኛ□· □□ን በእምነት የተሰጠ መረጃን የያዘ ከሆነና የመረጃው መገለፅ በውል ወይም በሌሎች ድርድሮች ላይ ሶስተኛ□·ን ወገን ተገቢ ላልሆነ ጉዳት ሊያጋልጠው ይችላል ወይም ሶስተኛ□·ን ወገን በንግድ ውድድር ሊጎዳው ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ያለ ከሆነ፣ የመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት አንድ መረጃ ሊከለከል የማይችለው መረጃው:-

ሀ/ ለህ□ብ ፅል□ እንዲሆን ተደርጎ ከሆነ፣

ለ/ ሶስተኛው ወገን በአንቀጽ 09 መሰረት ፈቃደኛነቱን የገለፀ ከሆነ ወይም ሶስተኛው ወገን በሌላ አኳኋን መረጃ□· ለ□□ቂ□· እንዲሰጥ በፅሑፍ የፈቀደ እንደሆነ ወይም

ሐ/ መረጃን በሰጠው በሶስተኛው ወገን በራሱ ወይም በሶስተኛ ወገን ስም ማንኛ□·ም □ተመረተ ነገርን ወይም የአካባቢ ደህንነት አስመልክቶ የተከናወነ ሙከራ ወይም የምርምር ስራን የሚመለከት ከሆነና የመረጃው መገለፅ በህዝብ ደህንነት ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማሳወቅ አስፈላጊ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ /ሐ/ የተመለከተው መረጃ የሙከራ ወይም የምርመራ □□ዎችን ለማዳበር የተደረጉ ቅድመ ሙከራዎችን ወይም ሌሎች ምርመራዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን አያካትትም፡፡

18. በእምነት የተሰጠ የሶስተኛ ወገን መረጃን ስለመጠበቅ

1/ የህዝብ ግንኙነት □ላ□□· □ተ□□ቀ□· መረጃ:-

ሀ/ የመንግስት አካል መገለጽ የሌለበት መረጃ ልውውጥን በሚመለከት ያደረገውን የውል ፅ□□ እንዲያፈርስ በማድረፅ በተዋዋዩ ወገን ክስ ሊያስመሰርትበት የሚችል ከሆነ □ጁም፣

ለ/ ሶስተኛ ወገን አይገለጽም ብሎ በማመን የሰጠውን መረጃ የሚመለከት ሆኖ □መረጃ□ መገለጽ ወደፊት ከተመሳሳይ ምንጭ የሚገኙ ተመሳሳይ መረጃዎችን መቀበልን ሊያስተጓጉል የሚችል ከሆነ እና፣ የመንግስት አካል ለህዝብ ጥቅም ሲባል መረጃዎቹን በየጊዜው መቀበል ያለበት ከሆነ፣ የመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ ይኖርበ□ል።

2/ የንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ ድን□ጌ ቢኖርም ሶስተኛው ወገን መረጃው ለመረጃ ጠያቂው እንዲሰጥ በጽሑፍ ከፈቀደ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው መረጃውን መስጠት ይኖርበታል።

## 19. ሶስተኛ ወገንን ስለማሳወቅና ጣልቃ ስለማስገባት

የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረበለት የመረጃ ጥያቄ ሶስተኛ ወገንን የሚመለከት ከሆነና መረጃውን በሙሉ ወይም በከፊል ለጠያቂው ለመስጠት ካሰበ ዓ□ቄ□ በ□ረሰ□ በ15 ቀናት ውስጥ መረጃውን የጠየቀውን ሰው ስም፣ የተጠየቀውን መረጃ ይዘት፣ እንዲሁም መረጃው መገለጽ ይኖርበታል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር መረጃው የሚመለከተው ሶስተኛ ወገን ተቃውሞ ካለው ይህንኑ ማስ□□ቂ□□ በ□□ በ15 ቀናት □ስዓ እንዲያቀርብ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

በተጠየቀው መሰረት ተቃውሞ አለማቅረብ የዚህ አዋጅ አንቀፅ 16 /2/ እና አንቀፅ 17 /2/ /ለ/ ድንጋጌዎች □□ትን ያስከትላል።

## 20. የግለሰቦችንና □ንብረት ደህንነት ስለመጠየቅ

የህዝብ ግንኙነት □ላ□□ □ተ□□ቀ□ መረጃ ቢ□ለ□:-

1/ የግለሰብን ሕይወት ወይም አካላዊ ደህንነት ለጉዳት ሊያገልጥ የሚችል ከሆነ፣

2/ የሕን□፣ □ጁም የኮምፒውተርና የሌላ መገናኛ መሣሪያን፣ ወይም የሕዝብ የማመላለሻ አገልግሎት የሌላ ማንኛውንም ዓይነት የንብረት መዋቅርን ወይም አሰራርን ደህንነት ሊያሰናክል ወይም ሊያደናቅፍ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ፣ ወይም

3/ በምስክሮች ጥበቃ ፕሮግራም የሚሸፈን ግለሰብን ወይም የጠቅላላውን ህዝብ ወይም አንድ የተወሰነ የህዝብ ክፍልን ደህንነት ለመጠበቅ የተበጁ ስልቶችን፣ እቅዶችንና አሰራሮችን ሊያደናቅፍ ወይም ሊያሰናክል የሚችል ከሆነ፣ መረጃን መግለጽ የለበትም፡፡

## 21. የህግ አስከባሪና የፍርድ ምርመራ ስራዎች ጥበቃ

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ ወይም መኖሩን ወይም አለመኖሩን እንዲያረጋግጥ የተጠየቀው መረጃ፣ የተፈጸመን ወይም ሊፈጸም የሚችል የህግ ጥሰትን መመርመሪያ፣ መከታተያ፣ መግቻ ወይም መከላከያ ዘዴዎችን፣ ቴክኒኮችን፣ የአሰራር ስነ-ስርዓቶችን ወይም የተግባር መመሪያዎችን የሚመለከት ከሆነና የመረጃው መገለጽ ለወንጀል አፈጻጸም ምቹ መረጃን በመፍጠር ውጤታማነታቸውን ሊያሰናክል ወይም ከህግ ማምለጥን ሊያስከትል የሚችል ከሆነ የመረጃ ጥያቄውን ሊከለከል ይችላል፡፡
2. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በተጠየቀው መረጃ የሚመለከተው የወንጀል ተጠርጣሪ ክስ ገና በዝግጅት ላይ ያለ ከሆነ ወይም ዝግጅቱ ቢጠናቀቅም ክሱ ገና ያልተጀመረ ከሆነ ወይም ክሱ በመታየት ላይ ያለ ከሆነና የተጠየቀው መረጃ መገለጽ ወይም መረጃው መኖሩን ወይም አለመኖሩን ማረጋገጥ፡-

   ሀ/ ክሱን ሊያሰናክል የሚችል፣

   ለ/ የፍትህ መጨናገፍን ሊያስከትል የሚችል ወይም

   ሐ/ የፍርድ ሂደቱን የሚዛናዊነት ወይም ገለልተኝነት ሊያዛባ የሚችል ከሆነ የተጠየቀው መረጃ መግለጽ አይኖርበትም፡፡
3. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው ሰንድ በቁጥጥር ስር ስላሉ ወይም በህግ ጥበቃ ስር ስላሉ ሰዎች አጠቃላይ የጥበቃ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎችን ብቻ የያዘ ከሆነ የመረጃ ጥያቄውን በዚህ አንቀጽ መሰረት ውድቅ ሊያደርግ አይችልም፡፡

## 22. በፍርድ ምርመራ ሂደት እንዳይገልጹ ጥበቃ ስለሚደረግላቸው መረጃዎች

የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የመንግስት አካልን ሰነድ ለማግኘት የቀረበው ጥያቄ በክስ ክርክር ላይ ተከራካሪ የሆነው ወገን ለሌላኛው ወገን እንዲገልጽ በህግ የማይገደድባቸውን መረጃዎች ለማግኘት የቀረበ ከሆነ የዚህ ልዩ መብት ተጠቃሚ የሆነው ሰው በመብቱ አልጠቀምበትም ካላለ በስተቀር መፍቀድ የለበትም፡፡

## 23. ስለመከላከያ የደህንነትና አለም አቀፍ ግንኙነት

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንዲሰጥ የተጠየቀውን ወይም መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ መገለጽ ወይም መረጋገጥ የሀገሪቱን መከላከያ የሀገርን ጸጥታና ደህንነት ወይም አለም አቀፋዊ ግንኙነትን ሊጎዳ የሚችል ከሆነ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት

2. የዚህ አንቀጽ የንዑስ አንቀጽ/1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው መረጃ፡-

ሀ/ የጠላትን እንቅስቃሴ ወይም ጠብ ጸብ አጫሪ ተግባር ለመቋቋም ከሚደረግ ዝግጅት ወይም የአማጽያንን ወይም የጠላትን እንቅስቃሴዎች ከመከታተል፣ ከመከላከል፣ ወይም ከመግታት ጋር የተያያዙ ግዳጆች ወይም ወታደራዊ ልምምዶች ወይም ወታደራዊ ታክቲኮች ወይም ስትራቴጂዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣

ለ/ የአማፂያንን ወይም የጠላትን እንቅስቃሴዎች ለመከታተል፣ ለመከላከል ወይም ለመምታት ወይም ለማንበርከክ ወይም ለመግታት የሚያገለግሉ የጦር መሳሪያዎችን ወይም ሌሎች አይነት መሳሪያዎችን ወይም ለጦር መሳሪያነት ወይም ለተመሳሳይ ተግባር እንዲያገለግሉ ታስበው የተነደፉ፣ የተበጁ፣ የዳባሩ፣ የተመረቱ ማንኛውንም ነገሮች ብዛት፣ አይነት፣ አቅም፣ ጉልበት፣ ደካማ ጎን፣ አሰራር፣ ብቃት፣ ዝግጁነት እንቅስቃሴ ወይም አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን፣

ሐ/ የማንኛውንም ሰራዊት ወይም የሰራዊት ክፍል ወይም ባላደረባ ወይም የአማጽያንን ወይም የጠላትን እንቅስቃሴዎች የመከታተል፣ የመቆጣጠር፣ ወይም የመግታት ኃላፊነት የተጣለበትን የማንኛውንም አካል ወይም ሰው ባህሪይ፣ ብቃት፣ ደካማ ጎን፣ ተግባራት፣ እምቅ ችሎታ፣ ስምሪት ወይም እንቅስቃሴ የሚመለከት መረጃን፣

መ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ)፣(ለ)፣(ሐ) እና (ረ) የተመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰቢያ፣ መገምገሚያና መያዣ ዘዴዎችን ወይም ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ መሳሪያዎችን፣

ሠ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል (ሀ) የተመለከቱ መረጃዎች ምንጭ የሆኑ የሚስጥር መረጃ አቀባዮችን እና ማንኛውም ሌላ የመረጃ ምንጭን ማንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን፣

ረ/ የሀገር መካለከያን ወይም የአማጽያንን ወይም የጠላትን እንቅስቃሴዎች ከመከታተል፣ ከመከላከል፣ ከማንበርከክ ወይም ከመግታት ጋር የተያያዙ የሌላ ሀገር መንግስታትን ወይም አለም አቀፍ ድርጅቶችን የሚመለከት ወይም በሀገሪቱ ወይም በሀገሪቷ ስም በአለም አቀፋዊ ምስክሮችና ውይይቶች ላይ ጥቅም ላይ የሚውልን የፀጥታ መረጃ (ኢንተለጀንስን) ሚመለከት መረጃን፣

ሰ/ በአለም አቀፍ ስምምነት ወይም ድርድር መሰረት ጉዳዩ በሚስጢር እንዲጠበቅለት ለሚፈልግ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም ሌላ መንግስት በሀገሪቱ ወይም በሀገሪቷ ስም የተሰጠ መረጃ፣

ሸ/ በአለም አቀፍ ስምምነት ወይም በአለም አቀፍ ልማዳዊ ህግ መሰረት በምስጢር መጠበቅ ያለበትን መረጃ፣

ቀ/ በሀገሪቱ ወይም በሌላ መንግስት ወይም አለም አቀፋዊ ድርጅት እየተደረጉ ባሉ ወይም ወደፊት በሚደረጉ አለም አቀፍ ድርድሮች ላይ በመንግስት ወይም በሌላ የውጭ ሀገር መንግስት ወይም የሚያዙ አቋሞችን የሚመለከት መረጃን፣ ወይም

በ/ ከሌላ መንግስት ወይም አለም አቀፍ ድርጅት ጋር የተደረጉ ዲፕሎማሲያዊ የመልእክት ልውውጦችን ወይም ከሀገሪቱ ዲፕሎማቲክ ሚስዮን ወይም ቆንጽላ ጽ/ቤቶች ጋር የተደረጉ ይፋዊ የመልእክት ልውውጦችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ያካትታል፡፡

## 24. የካቢኔ ሰነዶች

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው ካቢኔው ለህዝብ በይፋ እንዲገለጹ ከወሰናቸው መረጃዎች በስተቀር በካቢኔ ሰነድ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ለማግኘት ወይም የመረጃውን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ የቀረበ ማንኛውም ጥያቄ መቀበል የለበትም፡፡
2. የህዝብ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እንደተጠበቀ ሆኖ የካቢኔ ሰነድ፡-

ሀ/ ለካቢኔ የተመሩ ማንኛውም ሰነድ ወይም ለካቢኔ መቅረብ የሚገባው በመሆኑ በመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ለካቢኔ እንዲመራ የተደረገ ሰነድን፣

ለ/ የካቢኔ ይፋዊ ሰነድን

ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ /ሀ/ ወይም /ለ/ የተመለከቱት ሰነዶች ግልባጭ ወይም ቅጅ ወይም አካል የሆነ ከነዚህ ሰነዶች የተወሰዱ ጥቅሶችን የያዘ ሰነድን ወይም

መ/ ቢገለጽ ካቢኔው በይፋ ካሳተማቸው ውሳኔዎቹ ውጭ ያሉ የካቢኔው ወይም የኮሚቴዎቹን ውሳኔዎች ወይም ውይይቶች እንዲያውቁ የሚያደርግ ሰነድን ያካትታል፡፡

25. የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ጥቅሞችና የፋይናንስ ደህንነት እንዲሁም የመንግስት ድርጅቶች የንግድ እንቅስቃሴዎች ስለሚመለከቱ መረጃዎች

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ ወይም መኖር ወይም አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ ቢሰጥ ወይም ቢገለጽ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ወይም የፋይናንስ ደህንነት ጉዳት ላይ ሊጥል የሚችል ከሆነ ወይም መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማስተዳደር ያለውን አቅም ሊያዳክም የሚችል ከሆነ መረጃውን ለመከልከል ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀሱ የተመለከቱት መረጃዎች፡-
   ሀ/ በስራ ላይ ያለው ገንዘብ፣ በቅንስናሽ ሳንቲሞች፣ በህጋዊ ጨረታ፣ በውጭ ምንዛሬ ተመን ወይም በውጭ ኢንቨስትመንት ላይ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል የፖሊሲ ለውጥ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ውጥንን፣
   ለ/ በስራ ላይ ያለው የብድር ወይም የወለድ ተመንን፣ የጉምሩክ ወይም የኤክሳይዝ ቀረጥን፣ የግብር ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግስት የገቢ ምንጮች የመንግስት የፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥርን፣ ወይም ክትትልን፣ የመንግስት ብድርን፣ የሸቀጦች ወይም የአገልግሎቶች ዋጋን ኪራዮችን የደመወዝ ወይም የቀን ክፍያዎችን ወይም ሌሎች ገቢዎችን የሚመለከቱ ቁጥሮችን መለወጥ ወይም እንዳለ የመቆየት ውሳኔ ውጥኖችን ወይም
   ሐ/ የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ ወይም ይዞታን የሚመለከቱ ውጥኖችን ወይም አለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶችን ያካትታሉ፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ /ሐ/ እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው መረጃ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /2/ "የመንግስት አካል" ትርጓሜ ውስጥ ለማይካተት ማንኛውም ሰው የመንግስት አካልን የአክሲዮን ድርሻ ወይም ጥቅም ለማስተላለፍ የተደረገ ስምምነትን ወይም አለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶችን ያካትታል፡፡
4. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው መረጃው አስቀድሞ ለህዝብ ይፋ ካልተደረገ ወይም መረጃው የሚመለከተው ወይም የመረጃው ባለቤት ሆነ ሌላ የመንግስት አካል መረጃው እንዲገለጽ በጽሁፍ ካልፈቀደ ወይም በመንግስት አካል ወይም በመንግስት አካል ስም የተደረጉ የምርት ወይም የአካባቢ ሙከራ ውጤቶችን ወይም ምርመራዎችን የሚመለከት መረጃ ሆኖ ቢገለጽ በህዝብ ደህንነት ወይም

በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊደርስ የሚችል ከባድ አደጋን የሚያጋልጥ ካልሆነ በስተቀር የተጠየቀው መረጃ፡-

ሀ/ የመንግስት ወይም የመንግስት አካላትን የንግድ ምስጢሮች የያዘ ከሆነ፣

ለ/ ከንግድ ምስጢሮዎች ባይካተትም መገለጻቸው የመንግስት ወይም የማንኛውም መንግስታዊ አካል ጥቅም ሊጎዳ የሚችል የፋይናንስ፣ የንግድ ወይም የቴክኒክ ወይም የሳይንስ መረጃዎችን የያዘ ከሆነ፣ ወይም

ሐ/ ቢገለጽ ማንኛውም የመንግስት አካል የሚደረገውን ንግድ ውድድር ሊጎዳ ይችላል ወይም የመንግስት አካል ከሌሎች ጋር በሚያደርጋቸው የውል ወይም የሌሎች ድርድሮች ተጠቃሚ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ፣ የመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 26. የመንግስት የስራ ሰነዶች

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የመረጃ ፈላጊው የተጠየቀውን መረጃ የያዘው ሰነድ፡-

   ሀ/ በህግ የተሰጠን ኃላፊነት ወይም ግዴታን ለመወጣት፣ የውሳኔ አሰጣጥን ወይም የፖሊሲ ቀረጻን ለማገዝ፣ የቀረቡ ወይም የተዘጋጁ አስተያየቶችን፣ ምክሮችን፣ ውሳኔ ሃሳቦች ወይም ሪፖርቶችን፣ የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን ጨምሮ የተደረጉ ምክክሮችን፣ ውይይቶችን ወይም ስብሰባዎችን የሚያትቱ ሌሎች ሰነዶችን የያዙ ከሆነ፣

   ለ/ ቢገለጽ ግልጽ የሆነ የሃሳብ ልውውጥን፣ ምክክርን፣ ሪፖርትን፣ የውሳኔ ሃሳብን ወይም ውይይትን በመገደብ በማንኛውም የመንግስት አካል ውስጥ ወይም በተለያዩ የመንግስት አካላት መሀከል የሚደረገውን የውይይት ወይም የምክክር ሂደት ሊገድብ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ፣ ወይም

   ሐ/ ቢገለጽ በዝግጅት ወይም በውጥን ላይ ያለን ፖሊሲ ያለጊዜው እንዲገለጽ በማድረግ የፖሊሲውን ስኬት የሚያሰናክል ውጤትን ሊያስከትል ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት አለ፣

   ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

2. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው ሰነድ

   ሀ/ የመንግስት አካላት የሚጠበቅባቸውን የቁጥጥር፣ የኦዲት የምርመራ ወይም የፍተሻ ቴክኒኮችንና ስነ-ስርዓቶችን የመሳሰሉ የውስጥ አሰራሮችንና መመሪያዎችን የያዘ ከሆነና የሰነዱ መገለጽ የመንግስት አካልን የሙከራ፣ የምርመራ ወይም የኦዲት አሰራሮችንና ዘዴዎችም ውጤታማነት ሊያስተጓጉል ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ፣

ለ/ ሰነዱ የግምገማ ሰነድ የያዘ ከሆነና መረጃውን ያቀረበው ሰው ማንነትና በሰነዱ ላይ የተገለጸ ቢሆንም ባይሆንም የመረጃው መገለጽ መረጃውን ለሰጠው ሰው መረጃው እንደማይገለጽ ወይም የመረጃ ሰጪው ማንነት በምስጢር እንደሚጠበቅ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተገባውን ቃል የማፍረስ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ፣ ወይም

ሐ/ ሰነዱ ማንኛውም የመንግስት አካል ኃላፊን ማስታወሻዎች ወይም የዝግጅት ሃሳቦችን ወይም ሌሎች ማንኛውንም አይነት ረቂቆችን የያዘ ከሆነ.

የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀት በንዑስ አንቀ ጽ /1/ እና /2/ የተመለከቱትን መረጃዎች የያዘ ሰነድ በፍርድ ምርመራ ሂደት ሊሰጡ የሚገባቸውን ማብራሪያዎች ወይም ምክንያቶች የያዘ እስከሆነ ድረስ መከልከል የለበትም፡፡

## 27. በጥቅሉ የቀረቡ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ አጠቃቀምን የሚያዛቡ፣ ወደፊት ታትመው የሚወጡ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚቀርቡ፣ የመረጃ ጥያቄዎች

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው፡-

1. ጥያቄው በጥቅሉ የቀረበ ከሆነ ወይም ከመጠናቸው ብዛት የተነሳ የተጠየቁትን መረጃዎች የመገልበጡ መደበኛ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀም የሚያዛባ ወይም የመንግስት አካሉን መደበኛ ስራ የሚያስተጓጉል ከሆነ፣
2. መረጃ ፈላጊው ተቀባይነት ሊያገኝ በሚያስችለው መልክ ያቀረበውን ጥቅል ጥያቄ እንዲያስተካክል የመረዳት ግዴታውን ቢወጣም አመልካቹ በጥቅሉ የቀረበውን ጥያቄ ያላስተካከለ ከሆነ፣
3. መረጃው በአንድ በተወሰነ ጊዜ እንዲታተም የሚያዝ፣ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያው ወይም ትእዛዙ ኖሮ የመረጃው ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ መረጃው ሊታተም የሚችል ከሆነ፣ ወይም
4. ለጠቅላላው ህዝብ እንዲዳተረሱ ታትመው በወጡ ህትመቶች ውስጥ መረጃው የተካተተ ከሆነ፣ መመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## 28. የህዝብ ጥቅም ማመዘን

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 16 እስከ 26 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በመረጃው መገለጽ ጥበቃ በተደረገላቸው ጥቅሞች ላይ የሚደርሰው ጉዳት በመረጃው መገለጽ ሊገኝ ከሚችለው ህዝብ ጥቅም የሚበልጥ ካልሆነ በስተቀር መረጃ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄ ውድቅ ማድረግ የለበትም፡፡

## 29. ተነጥሎ ስለሚሰጥ መረጃ

በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ሊከለከሉ የሚችሉ ወይም መከልከል ያለባቸውን መረጃዎች አካቶ የያዘን የመንግስት አካል ሰነድ ለማግኘት ጥያቄ ሲቀርብ መገለጽ የሌለባቸውን የሰነዱ ክፍሎች ወይም ገጾች ክልከላው ከሚመለከታቸው ገጾች ነጥሎ ማውጣቱ አስቸጋሪ ካልሆነ በስተቀር ክልከላ ያልተደረገባቸው የሰነዱ ክፍሎች መገለጽ አለባቸው፡፡

## 30. መረጃው የሚሰጥበት ቋንቋ

ለመንግስት አካል የቀረበው የመረጃ ጥያቄ የተፈቀደለት አመልካች የጠየቀው መረጃ፡-

1. በመረጠው ቋንቋ የተዘጋጀ ከሆነ መረጃው አመልካቹ በመረጠው ቋንቋ ይሰጠዋል፡፡
2. መረጃው አመልካቹ በመረጠው ቋንቋ ያልተዘጋጀ ከሆነ መረጃው በተዘጋጀበት ቋንቋ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

## 31. በመረጃ ክልከላ ላይ ይግባኝ ስለማቅረቡ

1. በዚህ ክፍል ስር ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት በህዝብ ግንኙነት ኃላፊው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለመንግስታዊ አካል የበላይ ኃላፊ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. አቤት ባዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አቤቱታውን በጊዜ ለማቅረብ አለመቻሉን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት ከቻለ ቅሬታ ሰሚው አካል በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ /1/ የተወሰነው ጊዜ ቢያልፍም የቀረበለትን የቅሬታ አቤቱታ ሊቀበል ይችላል፡፡
3. አቤቱታው የቀረበለት መንግስታዊ አካል የበላይ ኃላፊ በ10 ቀናት ውስጥ በአቤቱታው ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
4. በመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም አመልካች ቅሬታውን ውሳኔ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 32. የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ኃላፊነቶች

1. የህዝብ እንባ የባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ የክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ለመጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቀላሉ የሚረዳው በሚችል አኳኋን፡-

ሀ/ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች አላማዎች፣

ለ/ የእያንዳንዱን የመንግስት አካል የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ እና የምክትሉ ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ሐ/ የእያንዳንዱን የመንግስታዊ አካል አብይ የስራ ጸባይ፣

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሰረት የሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች አቀራረብና የሚቀርቡበትን ፎርም፣

ሠ/ መረጃ ጠያቂዎች በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት መሰረት ከህዝብ ግንኙነት ኃላፊው ስለሚደረግላቸው ትብብር ወይም አገልግሎቶች፣

ረ/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ለመረጃ ጠያቂዎች ስለሚሰጠው እገዛ ወይም አገልግሎት

ሸ/ በዚህ አዋጅ በክፍል ሶስት ድንጋጌዎች የተመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች ባልተከበሩ ጊዜ በአዋጁ የተበጁ መፍቴሂዎችን፣

ቀ/ ስለ አስዳደራዊ ይግባኞች አቀራረብ፣

በ/ የህዝብ ግንኙነት ወይም የመንግስታዊ አካላት ኃላፊዎችን ውሳኔ በመቃወም ለፍርድ ቤቶች ስለሚቀርቡ የይግባኝ ማመልከቻዎች

ተ/ በዚህ ክፍል በመንግስት አካላት ታትመው እንዲወጡ ስለታዘዙ መረጃዎች ዝርዝር ማብራሪያና እነዚህን ማብራሪያዎች ለማግኘት የተበጁ ስነ-ስርዓቶችን፣

ቸ/ የመረጃ ክፍያ ስለሚከፈልባቸውና ከክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነጻ ጥያቄዎች ፣ እና

ነ/ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች በተመሳሳይ መንገድ እንዲፈጽሙ ለማድረግ የሚወጡ የአፈጻጸም መመሪያዎችንና ማብራሪያዎችን የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት በስራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ ባሉት 18 ወራት ጊዜ ውስጥ በመንግስት ኦፊሲያል ቋንቋዎች አትሞ የማውጣት ኃላፊነት አለበት፡፡

2. የህዝብ እንባ ተባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ ከተሰጡት ስልጣኖችና ኃላፊነቶች በተጨማሪ አቅም በፈቀደ መጠን፡-

ሀ/ በአንቀጽ 31 (1) የተቀበላቸውን ሪፖርቶች መሰረት በማድረግ የዚህ ክፍል ደንጋጌዎች በመንግስት አካል መፈጸማቸውን የመከታተልና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፣

ለ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አፈጻጸም አስመልክቶ አሰራሮችን ለማዳበር እና ለማሻሻል የሚረዱ አጠቃላይ ወይም ዝርዝር የውሳኔ ሃሳቦችን ለመንግስታዊ አካላት የማቅረብ፣

ሐ/ መረጃን የማግኘት መብትንና የዚህን ክፍል ድንጋጌዎቸ ውጤታማ አፈጻጸም አስመልክቶ ለህዝብ ግነምኙነት ኃላፊች የሚሰጡ ስልጠናዎችን የማዘጋጀት ወይም የማገዝ

መ/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የሚጠየቁ መስፈርቶችንና ግለሰቦች ያላቸውን መብት የማሳወቅ

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት ታትመው መውጣት ያለባቸውን መረጃዎች በተመለከተ ከስራ ባህሪያቸው የተነሳ በአንድ ህትመት ውስጥ መረጃዎቻቸውን አጣምረው ማውጣት ያለባቸውን የመንግስት አካላት ወይም የህትመት ወጪን መጋራት የሚኖርባቸውን የመንግስት አካላት ወይም ወጪያቸው በሌላ በመንግስት አካል ሊሸፈንላቸው የሚገባ የመንግስት አካላትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን መስጠት፣

ረ/ የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ድንጋጌን አጠቃቀም ግልጽ ለማድረግ የሚያግዙ የማብራሪያ መድብሎችን የማዘጋጀት፣

ሰ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማሻሻል ለማጠናከርና ለማዳበር የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፣ እና

ሸ/ ለዚህ ክፍል ድንጋጌዎች አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፣ ስልጣንና ኃላፊነት አለው፡፡

3. የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችለው የተሟላ ስልጣን ያለው ሲሆን ለስራው የሚያስፈልገውን ተጨማሪ በጀትም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያገኛል፡፡
4. ዋና እንባ ጠባቂው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## 33. አስተዳደራዊ ይግባኝ

1. ዋና እንባ ጠባቂ በአንቀጽ 31/4/ መሰረት ቀረቡለትን የይግባኝ ቅሬታዎች ሲመረምር በአንቀጽ 35 መሰረት መገለጽ የሌለባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ሰርተፍኬት ከተሰጣቸው ሰነዶች በስተቀር በመንግስት አካላት እጅ የሚገኙ ማንኛቸውንም ሰነዶች አስቀርቦ መመርመር ይችላል፡፡ ዋና እንባ ጠባቂው ይህንን ሲያከናውን በዚህ አዋጅ እንዳይገለጹ ክልከላ የተደረገባቸው መረጃዎች አለመገለጻቸውን ማረጋገጥ ግዴታ አለበት
2. ዋና እንባ ጠባቂው በአንቀጽ 31/4/ መሰረት በቀረበለት የይግባኝ አቤቱታ ላይ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት

3. ዋና እንባ ጠባቂው አቤቱታውን ውድቅ የማድረግ ወይም መንግስታዊ አካል የተጠየቀውን መረጃ እንዲሰጥ የመወሰን ወይም መንግስታዊ አካል በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታዎች እንዲያሟላ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘውን እርምጃ የመውሰድ ስልጣን አለው፡፡

## 34. ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ይግባኝ

1. በዋና እንባ ጠባቂው በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው መረጃ የፌደራል የመንግስት አካልን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ይግባኙን ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መረጃው የክልል የመንግስት አካልን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ደግሞ ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በሰላሳ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የይግባኝ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት በአንቀጽ 35 መሰረት ሰርተፊኬት ከተሰጠባቸው ሰነዶች በስተቀር ማንኛውንም ሰነድ ሊመረምር ይችላል፡፡ በማንኛውም ምክንያት እነዚህ ሰነዶች ለፍርድ ቤቱ እንዳይቀርቡ ማድረግ አይቻልም፡፡
3. ፍርድ ቤት የሚያደርገው የፍርድ ምርመራ፣ በዚህ አዋጅ መሰረት መገለጽ የሌለበትን ማንኛውንም መረጃ መግለጽ የለበትም፡፡ ፍርድ ቤቱ መረጃዎቹ እንዳይገለጹ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አቤቱታ አቅራቢው ወይም ወኪሉ በሌለበት ማስረጃ መቀበልም ሆነ ክርክር መስማት ይችላል፡፡
4. ፍርድ ቤቱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ከሚሰጠው ውሳኔ በተጨማሪ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 35. ሰርተፊኬት ስለመስጠት

1. እንዲሰጥ የተጠየቀው ወይም መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ ብሄራዊ ጸጥታን መከላከያን ወይም አለም አቀፍ ግንኙነትን የሚመለከት ሲሆን የመንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች መረጃው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 ክልከላዎች የሚሸፈንና የማይፈቀድ መረጃ መሆኑና መረጃ ቢገለጽ በሀገር ደህንነት ላይ እርግጠኛ የሆነ አደጋ ሊከሰት የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዋናው እንባ ጠባቂውም ሆነ ማንኛውም ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ /1/ መሰረት ሰርተፊኬቱ የተሰጠው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን የመመርመር ስልጣን የላቸውም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ /1/ መሰረት በመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ የተሰጠ ሰርተፊኬት ትክክለኛ ቅጂ ከተሰጠ ጀምሮ ባለው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰርተፊኬቱን የማጽደቅ ወይም መሰረዝ ስልጣን አለው፡፡

## 36. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

1. የእያንዳንዱ መንግስት አካል የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የዚህን አዋጅ ክፍል ሶስት ለማስፈጸም ያከናወናቸውን ተግባራት አመታዊ ሪፖርት ከግንቦት 30 በፊት ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት የሚዘጋጀው ሪፖርት፡-
   ሀ/ ለመንግስታዊ አካሉ የቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎችን ብዛት፣
   ለ/ በከፊልና በሙሉ ተቀባይነት ያገኙ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት፣
   ሐ/ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያገኙ መረጃ ጥያቄዎች ብዛት፣
   መ/ በመንግስታዊ አካሉ የተሰጡ የውስጥ ይግባኝ መፍትሄዎችና በነዚህ መፍትሄዎች መሰረት ተቀባይነት ያገኙ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት፣
   ሠ/ ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የቀረቡ ይግባኞችን ብዛትና የውሳኔዎቹን ውጤቶች
   ረ/ ፍርድ ቤት የቀረቡ ይግባኝ ጥያቄዎችን ብዛትና የውሳኔዎቹን ውጤቶች፣
   ሰ/ እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን፣ የሚይዝ ይሆናል፡፡
3. የእያንዳንዱ መንግስታዊ አካል የበላይ ኃላፊ የፌደራል መንግስታዊ አካል ከሆነ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የክልል መንግስት አካል ከሆነ ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልል አስተዳደር ምክር ቤት አመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ ተመለከተውን ሪፖርትም አለካቶ ማቅረብ አለበት፡፡

## 37. ደንብ የማውጣት ስልጣን

ሚኒስቴሪች ምክር ቤት፡-

1. ለተለያዩ የመረጃ አይነቶች ተፈጻሚ ስለሚሆነው የክፍያ ተመን ሰንጠረዥ፣ ክፍያዎች ስለሚቀነስበት ወይም መረጃ በነጻ ስለሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታ፣

2. ስለተከለከሉ መረጃዎች አጠባበቅና ምደባ ወይም ሚስጥርነታቸው ስለሚቀርበት ሁኔታ፣ እንዲሁም
3. በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ውስጥ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን አፈጻጸም ለማሟላት የሚያስፈልጉ ማንኛቸውንም ጉዳዮች የሚመለከቱ፣ ደንቦች ያወጣል፡፡

## 38. ስለ ሰነድ አጠባበቅ

1. የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሚመለከታቸውን ወገኖች በማማከር ስለ ሰነዶች አጠባበቅ፣ አስተዳደርና አወጋገድ የተግባር መመሪያ ያወጣል፣ መመሪያውን ከጊዜው ጋር ለማጣጣምም በየጊዜው አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ያደርጋል፡፡
2. ማንኛውም የመንግስት አካል በእጁ የሚገኙ ሰነዶችን በዚህ አንቀጽ /1/ በተመለከተው ተግባር መመሪያ መሰረት መጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የመንግስት አካል የግል መረጃዎችን ለማስተካከል የሚያስችል በቂ አሰራር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፡፡

## 39. ልዩ ልዩ ጉዳዮች

1. በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ውሰጥ የተመለከቱትን ግዴታዎችና ኃላፊነቶችን በቅን ልቦና ለመፈጸም በተደረገው ማንኛውም አይነት ድርጊት በማንኛውም ሰው ላይ የፍትሀ ብሔር ወይም የወንጀል ኃላፊነት አይኖርም፡፡
2. ማንኛውም ሰው የህግ ወይም የስራ ግዴታን በመተላለፍ ጥፋትን ወይም የህዝብ ጤንነትን፣ ደህንነትን ወይም የአካባቢያዊ ደህንነትን ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን የሚመለከት መረጃን በመግለጹ ለህጋዊ ወይም አስተዳደራዊ ቅጣቶች የማይዳርገው፣ መረጃዎቹ በእርግጥም ጥፋትን ወይም የህዝብ ጤንነትን፣ ደህንነትን ወይም አካባቢያዊ ደህንነትን ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን ሊያሳዩ ይችላሉ የሚል ምክንያታዊ እምነት በመያዝ ድርጊቱን በቅን ልቦና የፈጸመው ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ አላማ ከግለሰብ ድርጊት ጋር ተያያዥነት ቢኖረውም ባይኖረውም ጥፋት ማለት የወንጀል ድርጊት፣ የህግ ግዴታን መተላለፍ፣ ፍትህ ማዛባት፣ ሙስና ማጭበርበር፣ በስልጣን ያለ አግባብ መጠቀም ወይም ከባድ የስነ ምግባር ጉድለት ማለት ነው፡፡
4. በዚህ ክፍል ውስጥ የተረጋገጡትን መረጃ የማግኘት መብቶች ለመጣስ በማሰብ ሆነ ብሎ ማንኛውንም ሰነድ፣

   ሀ/ ያጠፋ፣ ያበላሸ፣ ወይም የቀየረ ወይም የደለዘ ወይም

ለ/ የደበቀ፣ በተንኮል የከለከለ ወይም

ሐ/ ያፋለሰ ወይም አነስተኛ ሰነድ የሰራ ፣

ማንኛውም ሰው የወንጀል ጥፋቱ በፍርድ ሲረጋገጥበት በገንዘብ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

5. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሰረት ማመልከቻው ከመቅረቡ 25 ዓመት አስቀድሞ የሆነን፣ የተፈጸመን፣ የተከሰተን ወይም የተደረገን ነገር የሚመለከት የመረጃ ጥያቄን ውድቅ ለማድረግ ሚችለው መረጃው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 16፣ 17፣ 18 እና 23 ድንጋጌዎች ውስጥ የማይሸፈን የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

6. ሙስናን ወይም ሌላ ህገ ወጥ አሰራርን የስራ አፈጻጸም ብቃት ጉድለትን፣ ግለሰብን ወይም የድርጅትን ቅሌት ለመሸፈን ማንኛውም ሰነድ በምስጢር እንዲያዝ መወሰን ክልክል ነው፡፡

# ክፍል አራት

## የመገናኛ ብዙሃን መብቶችና ግዴታዎች

### የእርማት ወይም መልስ የመስጠት መብት

1. በመገናኛ ብዙሃን በቀረበ የፍሬ ነገር ዘገባ መልካም ስሙና ክብሩ የተጎዳበት ማንኛውም ሰው ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙኃን ላይ ያለ ክፍያ መልስ የመስጠት መብት አለው፡፡

   ሀ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ዋና አዘጋጅ ወይም ምክትል የተላከለትን ምላሽ እለታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ3 ቀናት ውስጥ፣ ሳምንታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ9 ቀናት ውስጥ ወይም በሌላ አይነት ህትመት ከሆነ በቀጣዩ እትም ያለእርማት የማውጣት ግዴታ አለበት፡፡

   ለ/ ለመልሱ መነሻ የሆነው ዘገባ የተላለፈው በቴሌቪዥን ወይም በሬዲዮ ፕሮግራም ከሆነ ኃላፊ የሆነው አዘጋጅ ምላሹ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ በቀጣዩ በፕሮግራሙ ክፍል ወይም በተመሳሳይ ፕሮግራም ያለ እርማት ምላሹን በነጻ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

   ሐ/ የሚቀርበው መልስ ከዘገባው ጋር የተያያዘ ተመጣጣኝና ህጋዊ ይዘት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

መ/ ዘገባው የተሰራጨው ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ /11/ (ሀ) እና (ለ) የተጠቀሰው የ3 ቀን የጊዜ ገደብ ወደ 24 ሰአት፣ የ14 ቀኑ ገደብ ደግሞ ወደ 38 ሰዓት ዝቅ እንደተደረገ ተቆጥሯል፡፡

ሠ/ የዚህ ንዑስ አንቀጽ /1/ /መ/ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ምላሹ ለመገናኛ ብዙኃኑ የደረሰው ምላሹ የሚወጣበት ህትመት ወይም ፕሮግራም ለመታተም ከመላኩ ወይም በአየር ከመለቀቁ ስድስት ሰዓታት ቀደም ብሎ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

2. መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ማንኛውም ሰው የህትመቱ ወይም የፕሮግራሙ አዘጋጅ ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ለማመልከት ይቻላል፡፡
3. ማመልከቻው የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔውን በ10 ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም በምርጫው ወቅት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻው በቀረበለት 24 ሰዓት ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
4. በወንጀል ህግ አንቀጽ 43 መሰረት ኃላፊ የሆነው ሰው መልሱን ለማውጣ ፈቃደኛ አለመሆኑን ከተረዳ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡
5. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 2000/49 የተመለከቱትን ከተፈታሚነት አያስቀሩም፡፡
6. በዚህ አሰነቀጽ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ /5/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ቅሬታ የፈጠረው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው ሶስት ወር ጊዜ ውስጥ መልስ የማውጣት ጥያቄው ለመገናኛ ብዙሃን የቀረበ ከሆነ ብቻ ነው፡፡
7. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ማንም ሰው እርሱን የሚመለከቱና በፍሬ ነገር ይዘታቸው ትክክለኛ ያልሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች እንዲታረሙለት ለማድረግ ባለው መብት ላይም በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

## ህጋዊ እርምጃዎችን ስለመውሰድ

### 41. ስለ ተጠያቂነት

1. በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ወይም የፍትሃ ብሄር ጉዳት በወንጀል ህግ አንቀጽ 43 በተደነገገው መሰረት ተጠያቂነት ካለባቸው ሰዎች ጋር የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቱ በተደራቢነት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡
2. በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለሚደርስ የስም ማጥፋት ጉዳት የፍታብሔር ክስ ከተመሰረተ እስከ ብር 100,000ሺ /አንድ መቶ ሺህ ብር/ የሚደርስ የህሊና የጉዳት ካሳ ሊወስድ ይችላል፡፡
3. በዚህ አዋጅ ክፍል አምስት እና ስድስት በተመለከቱ ድንጋጌዎችና በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሀከል ግጭት ከተፈጠረ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
4. የወንጀል ክሱ በይርጋ ቢታገድም ሆነ ውድቅ ቢደረግ እንኳን በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት ለደረሰ ጉዳት የፍትሀብሔር ክስ ሊቀርብ ይችላል፡፡

### 42. የእገዳ እርምጃዎችን ስለመውሰድ

1. በሌላ ህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ከተደነገገው ውጪ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መጽሐፍ ሊታገድ ይችላል፡፡
2. እንደነገሩ ሁኔታ የፌደራል ወይም የክልል አቃቤ ህግ በብሄራዊ ደህንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የሚችል ግልጽና ድርስ ሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በየጊዜው የሚወጣ ህገ ወጥ ህትመት ወይም መጽሐፍ ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የህትመት ውጤቱ እንዳይሰራጭ ፍርድ ቤት እንዲያዝ ማመልከት ይቻላል፡፡
3. አቃቤ ህግ ከነገሩ አጣዳፊነት የመነሳት ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መጽሐፍ እንዲታገድ ትእዛዝ መስጠት ይቻላል፡፡ ሆኖም አቃቤ ህግ አንድን በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መጽሐፍ ከስርጭት እንዲታገድ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው በተሰጠ በ48 ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ህጉ የእገዳ ማስታወቂያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ የእገዳ እርምጃውን የሚያጸድቅ መሆኑ አለመሆኑን በውሳኔ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መጽሐፍ እንዲታገድ በአቃቤ ህግ የተሰጠው ትዕዛዝ ሲቀርብለት፡-

   ሀ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መጽሐፍ ህገ-ወጥና ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ካገኘው አአቃቤ ህጉን ትእዛዝ በማጽደቅ አቃቤ ህጉ የማገድ እርምጃ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ክሱን እንዲመሰረት ወይም ህትመቱ እንዲወረስ ማመልከቻ እንዲያቀርብ ማዘዝ አለበት፡፡ አቃቤ ህግ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ካልፈጸመ ፍርድ ቤቱ በጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መጽሐፍ እንዲያዝና ስርጭቱም እንዲቋረጥ የሰጠውን ትእዛዝ ያነሳል፡፡

   ለ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መጽሐፍ ህግን የማይተላለፍና ከፍተኛ ጉድለት የማያስከትል ሆኖ ካገኘው በአቃቤ ህጉ የተሰጠውን የእገዳ ትእዛዝ ውድቅ በማድረግ የታቀደው ህትመት እንዲለቀቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትእዛዝ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ካልታገደ በስተቀር ትእዛዙ በተሰጠ በ72 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ይፈጸማል፡፡

5. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መጽሐፍ ላይ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ ወይም ውጤቱ እንዲወረስ ማመልከቻ ከቀረበ ፍርድ ቤቱ ህትመቱ እንዲያዝና እንደየአስፈላጊነቱ ቀጣይ እትሞችን ከማውጣት እንዲታገድ ወይም የህትመት ስራው እንዲወረስ ሲወሰን ወይም በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት የህትመቱ ስርጭት እንዲታገድ የሰጠውን ውሳኔ ለመሰረዝ ይቻላል፡፡

6. በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ወንጀል ከተፈጸመና በወንጀል ህግ መሰረት ኃላፊ የሚሆነው ሰው ካልተገኘ የግል ተበዳዩ ወይም አቃቤ ህጉ የወንጀል ክስ ከሚመሰረት ህትመቱ እንዲወረስ ለፍርድ ቤቱ ማመልከት ይችላሉ፡፡ ለወንጀሉ ኃላፊ የሚሆነው ሰው በሃገር ውስጥ መጥሪያ ለመስጠት በማይቻልበት ጊዜም በተመሳሳይ ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል፡፡

7. በእገዳው ከሚሸፈነው ጉዳይ ባህሪ ወይም በሌላ በቂ በሆነ ምክንያት የተነሳ አቃቤ ህጉ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /4/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ክሱን ለማቅረብ የማይችል ከሆነ በአቃቤ ህጉ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ የክስ ማቅረቢያ ጊዜውን እስከ ሁለት ሳምንት ሊያራዝመው ይችላል፡፡

8. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መጽሐፍ ስርጭት ላይ የሚሰጥ የእገዳ ትዕዛዥ ለትዕዛዙ መነሻ የሆነውን አንቀጽ ወይም አንቀጾች የህትመቱን ቅጽ፣ ጽሁፉ የወጣበትን እትም መግለጽ አለበት ፡፡

9. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት እና መጽሐፍ ላይ የሚሰጥ እገዳ ለስርጭት በተዘጋጁ ህትመቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የእገዳ ትእዛዙ በፖሊስ አማካይነት ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡
10. አቃቤ ህጉ በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ስልጣን አግባብ በሌለው መንገድ የተጠቀመበት እንደሆነ በገህግ ይጠየቃል፡፡

## 43. ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዙ ክሶች ስለሚቀርቡበትና ስለሚሰሙበት ሁኔታ

1. በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ወንጀል ድርጊት በመፈጸም የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ጠቅላይ አቃቤ ህጉ ካልወሰነ በስተቀር በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 59/2/ እና /3/ ድንጋጌዎች እንዲቆይ ሳይደረግ ክሱ በቀጥታ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡
2. ክሱን ለመስማት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻው በቀረበለት በ15 ቀናት ውስጥ ክሱ እንዲሰማ ማድረግ አለበት
3. ፍርድ ቤቱ ክሱ ከመሰማቱ ቢያንስ ከአምስት ቀናት በፊት የክሱን ማመልከቻ ግልባጭ ወይም ቅጂ እንዲሁም የቀረቡ ማስረጃዎች ካሉ ለተከሳሹ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡
4. ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት ክሱ መሰማት ከጀመረበት ቀን አንስቶ እጅግ ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፍርድ መስጠት ይኖርበታል፡፡
5. ተከሳሹ በአድራሻው ባለመገኘቱ የተነሳ መጥሪያውን ለማድረስ ያልተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በ7 ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን የሚገልጽ መጥሪያ በጋዜጣ እንዲወጣ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡
6. ተከሳሹ በሌለበት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 44 መሰረት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
7. የወንጀል ክስ ለመመስረት የግል ተበዳይ አቤቱታ ከማያስፈልጋቸውና በህገ መንግስቱ በተቋቋሙ የህግ አውጪ፣ የህግ አስፈጻሚ ወይም የፍርድ ቤቶች ባለስልጣኖች ላይ ከሚፈጸሙ ስም ማጥፋትና የሃሰት ወንጀል ድርጊቶች በስተቀር በግለሰቦችና በግል ድርጅቶች ላይ በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የሚፈጸሙ የስም ማጥፋትና በሃሰት የመወንጀል ክሶች በራሳቸው በግል ተበዳዮች መቅረብ አለባቸው፡፡
8. ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የሰጠውን ውሳኔ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ማስታወቂያ ቢሮ እንዲደርሰው ማዘዝ አለበት፡፡

## 44. ስለ ይግባኝ

1. በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤትም አመልካቹ ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ የፍርዱን ግልባጭ ለአመልካች መስጠት አለበት፡፡
2. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ በቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት

## 45. ስለ ቅጣት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7/1/ እስከ /3/ የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 20.000 /ሃያ ሺህ ብር/ ባላነሰ ከብር 200.000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
2. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 6/2/ን በመተላለፍ ሃላፊነት የሚቀበል አዘጋጅ ያልሰየመ ወይም በአንቀጽ 9/6/ የተደነገገውን ግዴታ የጣሰ ወይም በአንቀጽ 10 የተመለከቱትን ግዴታዎች ያላሟላ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አሳታሚ ወይም ብሮድካስተር እስከ ብር 15.000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 40 መሰረት በህትመቱ ላይ እንዲያወጣው የተላከለትን መልስ ወይም ማስተካከያ ያላወጣ ዋና አዘጋጅ ወይም የፕሮግራም አዘጋጅ እስከ 10.000 /አስር ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡ ጥፋት የተፈጸመው በምርጫ ወቅት ከሆነ እስከ ብር 15.000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
4. በዚህ አዋጅ የአንቀጽ 6/1/ ወይም የአንቀጽ 8 ድንጋጌን የተላለፈ ማንኛውም ሰው እስከ ብር 15.000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
5. በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በተፈጸም ወንጀል ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጠ የጥፋተኝነት ውሳኔው ታትሞ እንዲወጣ ሲደረግ ፍርድ ቤቱ ውሳኔው በህትመቱ ላይ እንዲወጣ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ወይም ህትመቶቹ እንዲያዙ ትእዛዝ የተሰጠበት የመገናኛ ብዙሃን ውጤት እንዳይሰራጭ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 46. ስለ ይርጋ

1. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 28/1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈጸሙ የወንጀል ጥፋቶች ህትመቶች ከተሰራጩበት ወይም ከተላለፉበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክሶች ካልቀረቡ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡
2. በብሮድካስት አማካይነት ለሚፈጸም ጥፋት ጥፋቱ የተፈጸመበት ፕሮግራም ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የወንጀል ክስ ካልተመሰረተ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 47. የአፈጻጸም ወሰን

1. ይህ አዋጅ በማንኛውም የህትመት ስራዎች ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል
   ሀ/ ለህትመት ስራው በዚህ አዋጅ መሰረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ከሆነ፣
   ለ/ የህትመት ስራው የተባዛ መሆኑን፤ የአሳታሚውን ወይም የአታሚውን ማንነት የታተመበትን አድራሻና አመተ ምህረት የሚገልጽ ጽሁፍ ያለበት ከሆነ ብቻ ነው፡፡
2. የህትመት ስራዎች እንደመገናኛ ብዙሃን የሚታዩት ተባዝተው ለስርጭት ወይም ለሽያጭ ሲቀርቡ ወይም ብሮድካስት ሲደረጉ ነው፡፡
3. በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከጽሁፍ ጋር አብሮ የወጣ ባይሆንም ማንኛውም ስእል እንደህትመት ስራ ይቆጠራል፡፡
4. በሽያጭ ወይም ያለክፍያ የተሰራጩ ማንኛቸውም ወሲብ ነክ ይዘት ባላቸው ህትመቶች ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ አይሆንም ስለዚህ የህትመት ስራዎች ስርጭትና ህትመት በሚመለከት ዝርዝሩ በሌላ በህግ ይወሰናል፡፡

### 48. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ተቋቁሞ የፕሬስ ስራ በማካሄድ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ፕሬስ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተመለከተው መሰረት መመዝገብና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡
2. አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ለማዘጋጀት ሲባል የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ከሁለት አመት በኋላ ሲሆን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል

## 49. ከአዋጁ ጋር ስለሚቃረኑ ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ትዝዛዝ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋክ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 50. ስለ ተሻሩ ህጎች

የዚህ አዋጅ ክፍል 3 ድንጋጌዎች በስራ ላይ እስከሚውሉበት ጊዜ ድረስ ተፈጻሚ ከሚሆኑት የፕሬስ አዋጅ ቁጥር 34/85 አንቀጽ 8 እና 19 በስተቀር ቀሪዎቹ የአዋጁ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

## 51. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡